ዮሐንስ

ቁጥር 27 | 2017 ዓ.ም



የሊዲያና
የስራ ስምምነት

የደራው
መጽሔት



ሙዳይ የበጎ
አድራጎት ማህበር
MUDAY CHARITY
ASSOCIATION

ተስፋን እንለግስ


ዕሮይ
ኦፕሬሽን
www.yederaw.com

ማውጫ

ምስሉን ሲጫኑት ወደ ፈለጉት ገጽ ይወስዶታል




የአሜሪካ ታሪፍ 11



ይገረም ተሾመ 22



በሰማይ በራሪ ታክሲ በአዲስ አበባ 15



ሊዲያና በአዲስ ስራ 19

ማውጫ


የቲክቶክ ውለታ 25


የሙዚቃው ዓለም ጦርነት 48


ወደብ ማግኝት 31


የመርካቶ አንባ 2 37


ርቀቱ በእጅ እና
በስልኮዎ መካከል ነው!
ባሉበት ሆነው እንወዳጅ
www.yederaw.com



የኛሬዉ

1ኛ ዓመት | መጋቢት 27 |ቁጥር አራት

+251919474444
www.yederaw.com
Magazine@Yederaw.com
አዲስ አበባ,ኢትዮጵያ

ማኔጂንግ ዳይሬክተር
ያፌት ገ/ህይወት(ምትኩ)

ዋና አዘጋጅ
ሰለሞን ከበደ
solomon@Yederaw.com

ም/ዋና አዘጋጅ
አቤኔዘር ወርቁ

ሪፖርተሮች
አሌኒ ግዛው
አያንቱ ሁንዴ

ፎቶግራፈሮች
ዳንኤል አበበ
ያሬድ ግስላ

ግራፊክስ ዲዛይን
አብርሃም ቦሪስ

ማርኬቲንግ
ልዕልት በላይነህ
marketing@Yederaw.com
+251919474444

ቴክኖሎጂ ዳይሬክተር
ሱራፌል ተፈሪ

ክሬቲቭ ዳይሬክተር
ያፌት ገ/ህይወት

ጸሐፊ
ምስጢር ጌታቸው

መሸ ተብሎ በር አይዘጋም!

ባንኮች እስከ ምሽት 3:30 ሰዓት ድረስ ክፍት እንዲሆኑ የሚያስገድደዉ ደንብ ከባንኮች አሰራር ጋር የማይጣጣም ነዉ ሲል የባንኮች ማህበር ተችቶታል። ማህበሩ ይህን ያለው ባሳለፍነው ሳምንት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ያወጣውን የደንብ ምክረ ሃሳብ ተከትሎ ነው።

ማህበሩ ባንኮች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አማካይነት የተለያዩ የባንክ አገልግሎቶችን ለደንበኞቻቸው በቀላሉ ማቅረብ እየቻሉ በመሆኑ፣ የምሽት አገልግሎት አላስፈላጊና አግባብነት የሌለው መሆኑን አንስቷል ።

ምንም እንኳን ማህበሩ እንዳለው ባንኮች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አገልገሎት በማቅረብ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን በጊዜ ያልተገደበ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ቢሆኑም ቴክኖሎጂው ከተደራሽነት አንፃር ውስንነት ይታይበታል። እንዲሁም ቴክኖሎጂን የመጠቀም የእውቀት ዝግጁነት ያላቸው ሰዎች ቁጥር ዝቅተኛነት ደግሞ ሌላው ተግዳሮት ነው።

ይህ ብቻ አይደለም ዛሬ ላይ ዓለም በከፍተኛ ፍጥነት የእድገት ጉዞ ላይ ትገኛለች። ለአብዛኞቹ ሃብታም ሃገራት ዛሬ ለደረሱበት የኢኮኖሚ ደረጃ ዋነኛውን ሚና የተጫወተው የሥራ ባህላቸው ነው። ያደጉ ሀገራት መሸ ብለው በራቸውን አይዘጉም።ፍላጎታቸውን ለማስፈፀም እንደ አለንጋ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ።

የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ መጎልበት በልቶ ከማደር በላይ ዋጋ አለው።ሀገራት ሉዓላዊነታቸውን ለመጠበቅ በኢኮኖሚ መበልፀግ አለባቸው።

ታድያ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ካደጉ ሀገራት የሥራ ባህልን መውሰድ አለባቸው። በተለይም አዲስ አበባ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን በጊዜ እና በቦታ ባለመወሰን የከተማዋን ኢኮኖሚ በማይዋዥቅ አለት ላይ ማፅናት አለባት። ባንኮች ከመደበኛ ሰዓት በላይ አገልግሎት እንዲሰጡ የተጀመረው እንቅስቃሴ የከተማዋን ኢኮኖሚ ከማነቃቃት በላይ የዘመናዊነት ባህሪን ያላብሳታል።

የባንኮች ማህበርም የከተማዋን መፃኢ እድል የተሻለ ለማድረግ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች ባለመገደብ የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይገባል።

የኣዘጋጆቹ መልዕክት!

የደራው መጽሔት

ፀሐይ አትጠፈጭም!


AD

የደራው ትኩረት

የአሜሪካ ታሪፍ መጨመር

“ የአሜሪካ ታሪፍ መጨመር፣ በኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል ” - አቶ ክቡር ገና

“ እርምጃው፣ ኢኮኖሚያዊ ጉዳትም ስለሚያስከትል፣ ሌሎች የገበያ መዳረሻዎችን ማፈላለግ ይገባል ! ”

የአሜሪካው ፕሬዝደንት ሰሞኑን ባደረጉት አዲስ የቀረጥ ጭማሪ እርምጃ፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ40 በላይ የአፍሪካ ሀገራትን አካቷል።

እርምጃው ኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ በምታስገባቸው ምርቶች ላይ የ10 በመቶ ቀረጥ እንዲጣልባቸው አድርጓል።

ይህ አዲሱ የፕረዝደንት ትራምፕ እርምጃ፣ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እና ወደ አሜሪካ ገበያ በሚገቡ የኢትዮጵያ ምርቶች ላይ ምን ተፅዕኖ ሊኖረው እንደሚችል ቲክቫህ ኢትዮጵያ የነጋገራቸው ባለሙያ፣ “ ተፅዕኖ መፍጠሩ አይቀሬ ነው ” ብለዋል።

የቀረጥ ወይም ታሪፍ ጭማሪው፣ ወደ አሜሪካ ገበያ የሚላኩ ሸቀጦች ዋጋቸውን ያንረዋል፣ ይህ ደግሞ በሸማቹ ማኅበረሰብ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው ሲሉ ተናረዋል፣ የኢኮኖሚ ባለሙያው አቶ ክቡር ገና።



በኢኮኖሚ፣ በንግድና ኢንቨስትመንት ጉዳዮች ትንታኔ በመስጠት የሚታወቁት አንጋፋው ባለሙያ አቶ ክቡር ገና በሰጡት ማብራሪያ፣ ኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ ከሞትልካቸው ምርቶች ቡና እና ጨርቃጨርቅ ትልቁን ድርሻ እንደሚይዙ ገልፀው፣ አሁን እነዚህ ምርቶች አሜሪካ በሚደርሱበት ጊዜ ዋጋቸው ይጨምራል ብለዋል።

የሸቀጦቹ ዋጋ ሲጨምር፣ ገዢዎቹ ይቀንሳሉ፣ ያ ደግሞ ሀገር ውስጥ ያሉ አምራቾች ምርታቸው ሊቀንስ እና በአቅምም ሊያንገዳግዳቸው ይችላል ሲሉም አክለዋል።

አቶ ክቡር ገና በዝርዝር ምን አሉ ?

“ እርምጃው የኤክስፖርት ኢኮኖሚውን ይጎዳዋል። ቀደም ሲል አባል የነበርንበት የአጎዋ ዕድል (የአፍሪካ ምርቶች ከቀረጥ ነፃ ወደ አሜሪካ ገበያ የሚገቡበት አሰራር) ተጠቃሚዎች ነበርን። ያ ዕድል ተቋርጦዋል።

የኢትዮጵያ ምርቶች ቀረጥ ተክፍሎባቸው ነበር ወደ አሜሪካ ገበያ ሲገቡ የነበሩት፡ ፡ አሁን የተጨመረው የ 10 በመቶ ታሪፍ ቀደም ብሎ በነበረው ላይ ነው።
ይህ የኢትዮጵያ ላኪዎችን ያዳክማል። በውጭ ምንዛሪ ግብይት ላይም ተፅዕኖ ይኖረዋል።

በአብዛኛው አንዲህ ዓይነት ለውጥ በሚመጣበት ጊዜ፣ የውጭ ምንዛሪ ግብይት (የገንዘብ መዘርዘሪያ መጠን) ላይ የሆነ ተፅዕኖ ያስከትላል። እርምጃው ብርን ሊያጠነክረው ይችላል፣ አለያም የበለጠ ሊያዳክመው ይችላል፣ እሱን ቀጥለን የምናየው ይሆናል፣ ግን ተፅዕኖው አይቀሬ ነው። ”

የትኞቹ ሸቀጦች የበለጠ ይጎዳሉ ?

“ በትክክል ምንድነው የሚፈጠረው የሚለው በትግበራው ወቅት ነው የሚታየው፡ ፡ ለምሳሌ እዛ ያሉት ኢምፖርተሮች (ከእኛ ላኪዎች ሸቀጦችን የሚረከቡ የአሜሪካ ነጋዴዎች)፣ አሁን በዚህ የታሪፍ መጨመር ምክንያት የሸቀጥ ዋጋ ጨምሮባቸዋል።

አሁን እነሱ ምን ይወስናሉ፣ ጭማሪውን ራሳቸው ሸፍነው ትርፋቸውን ቀንሰው እቃውን ለሸማች ያቀርባሉ ወይስ ጭማሪውን በቀጥታ ለተጠቃሚው ያስተላልፋሉ የሚለው ገና የሚታይ ይሆናል።

ለምሳሌ በአሜሪካ ገበያ ብዙም ተወዳዳሪ የሌለው የኢትዮጵያ ሽቀጥ ብዙም ተፅዕኖ ላይደርስበት ይችላል፣ ምክንያቱም ሸማቹ አማራጭ ስለሌለው ዋጋውም ቢጨምርበት እቃውን ይገዛዋል።

የሆነ ሆኖ ግን ታሪፉ የምርት ዋጋ እንዲጨምር ያደርጋል፣ ያ ደግሞ በሸማቾች ዘንድ የመግዛት ፍላጎት ይቀንሳል፣ ከዛም የምርት መጠን ይዳከማል፣ ገዢ ከሌለ የኢትዮጵያ አምራቾች ሊያመርቱ አይችሉም። ”

መፍትሔው ምንድነው የሚሆነው ?

“ መፍትሔው ያንን የሚተካ ሌላ ገበያ መፈለግ ነው። ከአሜሪካ ወጥቶ የሌሎችን ሀገራት ገበያ ማፈላለግ አስፈላጊ ይሆናል። ተፅዕኖው ከመበርታቱ በፊት ሌሎች የንግድ መዳረሻዎችን ማፈላለግ ይገባል።

ታሪፉ የተጣለው በሁሉም ሀገራት ላይ ስለሆነ፣ የትኛው ሀገር የበለጠ ይቋቋመዋል የሚለው ገና በትግበራ ወቅት የሚታይ ይሆናል። የታሪፍ ለውጥ መምጣት የፖሊሲ ለውጥ ለማድረግም ይረዳል።

ወደ ሌሎች ዘርፎች እንድነገባ ሊያስገድድ ይችላል። ለምሳሌ የቱሪዝም ዘርፉን ማጠናከርና ማስፋፋት ይገባ ይሆናል። በተጣለው ታሪፍ ምክንያት የሚታጣውን ገቢ ለማካካስ ማለት ነው።

በቅድሚያ ግን የእርምጃውን ተፅዕኖ በደንብ ማጥናትና የመውጫ መንገዶችን ማሰብ ተገቢ ነው። ተፅዕኖው ምን ሊሆን እንደሚችል ማየት ይኖርብናል። ”




የጋራ
ቀዜማ
ትጋት ነው!



የኢትዮጵያ አየር መንገድ በራሪ ታክሲ እውን ለማድረግ የሚያስችል ስምምነት አደረገ

ሰዎች በትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት ሰዓታቸው ሲቃጠል እያዩ ስለ በራሪ ታክሲዎች ማሰባቸው አይቀሬ ነው።

ለብዙ አስርት ዓመታት በራሪ መኪናዎች በሳይንስ ልብ ወለድ ፊልሞች እና በወደፊት ትንቢቶች ምልክት ሆነው አገልግለዋል።

 ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ግኝቶች ቢኖሩም የአየር ላይ ተሽከርካሪዎች ለብዙ ሰዎች ህልም መስለው ቆይተዋል።

ብዙ ሰዎችን የሚያስተናግዱ በረራ መኪናዎችን መስራት አሁንም ሊደረስበት የማይችል ቢመስልም ፣ ትናንሽ የአየር መጓጓዣዎች ሀሳብ ግን ከጥንት ጀምሮ ነበር።

ይሁን እንጂ እነዚህ ፈጠራዎች እንደ ታክሲ ሆነው ያገለግላሉ የሚለው ሐሳብ ጥቂት ዓመታትን ያስቆጠረ ነው።

እ.ኤ.አ. በጥቅምት 2022 ዊስክ የተሰኘ የንግድ ኩባንያ በአለም ላይ እጅግ የተራቀቀውን 6ኛ ትውልድ የአየር ታክሲ ይፋ አደረጉ። ስራው ጥብቅ የንግድ ደህንነት ደንቦችን ያሟላ ነበር።

የቻይናው ኤክስ ፔንጅ ሞተርስን ጨምሮ ሌሎች የተሸከርካሪ አምራቾች ተመሳሳይ ፅንሰ-ሀሳቦችን ማቅረብ ጀመሩ።

ኤክስ ፔንጅም ኢቪቲኦኤል የተሰኘ በራሪ በኪና አመረተ። እ.ኤ.አ. በ 2024 ኩባንያው የበረራ መኪናውን ለሕዝብ አስተዋወቀ።

ይህ ሁኔታ ከበለጸጉ ሀገራት የቴክኖሎጂ እድገቶች ጋር ለመራመድ ከሚታገሉት ከበርካታ የአፍሪካ ሀገራት የራቀ ሀሳብ ቢመስልም በቅርቡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከአሜሪካው አርቸር አቪዬሽን ጋር በምስራቅ አፍሪካ ሀገር የኤሌትሪክ አየር ታክሲ አገልግሎት ላይ ለመስራት ተስማምቷል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መኪናዎች ሀሳብን ወደ መሬት ለማውረድ ማቀዱና በስምምነቱ መሰረት አራት ተሳፋዎች የሚይዝ ፈጣን እና የአጭር ርቀት በረራዎች ማድረግ የሚችል የአየር ላይ ታክሲ ሊጠቀም እንደሆነ ተነግሯል።

የስምምነቱ ዋና ዓላማ ትራፊክ መጨናነቅን መቀነስ እና የካርቦን ልቀትን ማስወገድ ነው ተብሏል።





በተጨማሪም ከ60-90 ደቂቃ የሚፈጁ የመኪና ጉዞዎች ከ10-20 ደቂቃ የኤሌክትሪክ አየር ታክሲ በረራዎች የሚሆኑ ሲሆን ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ዘላቂነት ያለው እንዲሁም አሁን ካሉት መጓጓዣዎች ጋር የሚጣጣም ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው መሆኑ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድም በቀጣይ በትራፊክ መጨናነቅ የሚቸገሩ የአፍሪካ ከተሞችን የሚጠቅም ሞዴል ሊፈጥር እንደሚችል ተጠቁሟል።

ለዚህ ስራ እንደ መሠረተ ልማት፣ ሕግና ገንዘብ መሰናክሎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ቢታመንም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ ኤሌክትሪክ አየር ታክሲዎች ትኩረት ማድረጉ በቴክኖሎጂው ዘርፍ አንድ እርምጃ መራመዱን የሚያሳይ ነው ተብሏል።

ይህ ጅምር በጎርፍ እና በድርቅ ምክንያት የተከሰተውን የምግብ እጥረት ጨምሮ በአህጉሪቱ በርካታ ፈተናዎችን ያስከተለውን የአየር ንብረት ጉዳት ሊቀንስ እንደሚያስችልም ተነግሯል።

credit:Ethiopian AirLine,gazette_plus

AD



የደራው

ገላ

በቅርብ ቀን



በአይነቱ ለየት ያለና ግዙፍ የውበት ማሰልጠኛ ማዕከል ተከፈተ

የሂየማን ሄርና የውበት መጠበቂያ ምርቶችን በማስመጣትናለአገራችን ተጠቃሚዎች በማቅረብ የረጅም አመታት ልምድያለው ዞማ ሄር በመባል የሚታወቀው ድርጅት አሁን ደግሞየውበት አጠባበቅ ሙያ ስልጠናን ለመስጠት ዞማ የውበት ማሰልጠኛ (ZOMA BEAUTY ACADEMY) በሚል ስያሜ የስልጠና ማዕከል ከፍቷል።

“ድርጅቱ በዘርፉ የረጅም ጊዜ ልምድና ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎችን፤ ጥራት ካላቸውና ዘመኑ የደረሰበትንየቴክኖሎጂ የእድገት ደረጃ ከሚያሞሉ የስልጠና መሳሪያዎችጋር በማቀናጀት ለትራንስፖርት ምቹ በሆነውና ቦሌ ብራስአካባቢ በሚገኘው ሪያለቲ ፕላዛ ህንፃ 10ኛ ፎቅ ላይ ውበትናምቾት ያለውን ግዙፍ የስልጠና ማእከል አቋቁሟል” ሲሉየድርጅቱ ባለቤትና ስራ አስኪያጅ አቶ አርአያ ሀጎስ ገልፀዋል።

የስልጠና ማእከሉ እውቅና ባገኘንባቸው የሜካፕ፣ የፌሻል፣የጥፍር እና የፀጉር ስራ እንዲሁም የአይላሽ እና የኦምብሬየሙያ ዘርፎች ስልጠናዎችን ለመስጠት ዝግጅቱን ማጠናቀቁየተገለፀ ሲሆን የድርጅቱን አላማና የስራ ክንውን ወደ ህዝቡተደራሽ ለማድረግ በማሰብ የማርኬቲንግና የማስታወቂያባለሙያ ሞዴል ሊዲያና ሰለሞንን የድርጅቱ አምባሳደር አድርጎሾሟል። አርቲስት ሊዲያና ባላት ጠንካራ የስራ ባህል፤ በመልካም ስነ ምግባርና፤ በከፍተኛ ጥረት እራሷን ለስኬትበማብቃት ለሴቶችና ወጣቶች መልካም አርአያ በመሆኗድርጅቱ አብሮት ሊሰራ መወሰኑን የተቋሙ አመራሮች በእለቱ ለተገኙ የዜና አውታሮች ገልፀዋል።


የሙያ ስልጠናዎችን ከመስጠት ባሻገር በዘርፉ ለመሰማራትፍላጎትና ራእይ ኖሯቸው በፋይናንስ እጥረት ምክንያት መማርያልቻሉ ሰልጣኞችን ለማገዝ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመነጋገርበአንስተኛ ቅድመ ክፍያ የዱቤ አገልግሎት አግኝተውየሚማሩበትን እድል አመቻችቷል። እድሉን ኂነተም ቴክኖሎጂስ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ከተባለ ተቋም ጋርበመተባበር ያመቻቸ ሲሆን ከሊዲያና ሰለሞን ጋር እንዲሁም ከኂነተም ቴክኖሎጂስ ኃላ/የተ/የግል ማህበር ይህንንምስምምነት ለማከናወን መጋቢት 26 ቀን 2017 ዓ.ም ረፋድ ላይበተቋሙ ዋና መስሪያ ቤት የፊርማ ስነስርአት ፈፅማል። ከዚህም በተጨማሪ በስነ ስርአቱ ላይ የተገኙ ታዳሚዎችና ተጋባዥ እንግዶች የተቋሙን ልዩ ልዩ ከፍሎችና የመማሪያ ግብአቶች እንዲጎበኙ ተደርጓል።







#ታሪካችን



The oil refinery in Assab, Ethiopia, built with the assistance of the USSR. 1975



አርቲስት ይገረም ደጀኔ የኪ ሃውሲንግ አምባሳደር ሆነ

አርቲስት ይገረም ደጀኔ የኪሀውሲንግ ፋይናንስ ሶሉሽን የብራንድ አምባሳደር ሆኖ ተሹሟል።

በፌርማ ስነ-ስርዓቱ ላይ እንደተገለጸው የአምባሳደርነት ፌርማው አርቲስት ይገረም ደጀኔ በኪ ሃውሲንግ ፋይናንስ ሶሉሽን ለቴሌቪዥን፤ቢል ቦርድ እና ሶሻል ሚዲያዎች ላይ ማስታወቂያዎች መስራትን ያጠቃልላል።

ኪ ሃውሲንግ ፋይናንስ ሶሉሽን ከአርቲስት ይገረም ደጀኔ ጋር የተለያዩ ማህበራዊ ግዴታዎቻችንን ለመወጣት እና ህዝቡ ጋር የነበረውን ተደራሽነት በተሻለ መልኩ ለማጎልበት የተለያዩ ስራዎችን በጋራ ለመስራት ስምምነቱን እንዳረገ ተነግሯል።

ኪ ሃውሲንግ ፋይናንስ ሶሉሽን “Economies of Scale” ላይ የተመሰረተ ሞዴል ቀርፆ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን የማህበረሰባችንን ክፍሎች የቤት ባለቤት እያደረገ እንደሚገኝ የተገለፀ ሲሆን

ወደ ገበያው ከተቀላቀለ በአንድ አመት ከስድስት ወር ውስጥ መቶዎችን በአዲስ አበባ ስድስት ሳይቶች እና በባህርዳር ከተማ የቤት ባለቤት አድርጓል ተብሏል።

በመርሀገብሩ ላይ እንደተገለጸው ኪ ሃውሲንግ ፋይናንስ ሶሉሽን እስካሁን ድረስ 2 ጊዜ የእጣ ማውጣት ስነስርአት አከናውኗል ።
በአሁኑ ሰዓትም 20,000 የሚደርሱ አባላት እንዳለው ገልጾ ኪ መንደር የተሰኘ የመኖሪያ መንደር ለመገንባት በዝግጅት ላይ እንደሚገኝም ተነግሯል።

የብዙኀኑ ችግር ቤት ማጣት ሳይሆን የቤት መግዣ ገንዘብ እጥረት መሆኑን በመረዳት አነስተኛ እና መካከለኛ ገቢ ላላቸው ሰዎች በተመጣጣኝ ቅድመ-ክፍያ እና አነስተኛ ወርሃዊ ቁጠባ ያለምንም ወለድ የቤት አቅርቦት እያቀረበ ይገኛል።

ተቋሙ በረጅም ዓመት የአከፋፈል ስርዓት፣ በ10 ዓመት ውስጥ 100,000 ቤት ፈላጊዎችን የቤት ባለቤት ለማድረግ በመንቀሳቀስ የሚገኝ አገር በቀል ድርጅት ነው።
በ83,145 ብር ቅድመ-ክፍያ እና ከ2,000 ብር በሚጀምር ወርሃዊ መዋጮ በአዲስ አበባ እና በዋና ዋና የክልል ከተሞች ውስጥ የቤት ባለቤት መሆን ቀላል ነው።





"ተስፋችንን እንጂ"





በአንድ የቲክቶክ ቪዲዮ ከመንገድ ፅዳት ሠራተኛነት ወደ ሞዴሊንግ ሥራ

በታይላንድ ባንኮክ በመንገድ ፅዳት ሥራ የምትኖር አንዲት ወጣት በሩስያዊው ፎቶግራፈር በተነሣችው ፎቶ አማካኝነት በአንድ ሌሊት በሀገሯ ካሉ ትላልቅ ብራንዶች የሞዴሊንግ ሥራ ዕድል አግታለች።

ታሪኳ የሚጀምረው ባሳለፍነው ወር ሲሆን የ28 ዓመት ወጣት እና የሁለት ልጆች እናት የሆነችው ናፓጂት በሥራ ላይ ሳለች ሴምዮን ሬዝቺኮቭ በተባል ሩስያዊ ፎቶ ከተነሣች በኋላ ነው።

ሳታስበው ድንገት በሥራ ላይ ሆና ያያትና በውበቷ የተደነቀው ይህ ፎቶግራፈር ከርቀት በሞሆን ፎቶ ያነሳታል፤ ከዛም ቀርቦ ካናገራት በኋላ ያነሣትን ፎቶ ያሳያታል፤ ይህ ሁሉ ሲሆን በስልኩ እየቀረፀ የነበረው ሴምዮን በኋላ ላይ ይህንን ቪዲዮ በቲክቶክ ገጹ ላይ አጋርቶታል።

ቪዲዮውም በፍጥነት ብዙዎች ጋር ይደርሳል፤ አብዛኛውም ሰው የመንገድ ፅዳት በሞትሠራው እንስት ባላት ውበት በመገረም ስለሷ ማወቅ ይፈልጋል።

ለተለያዩ ሚዲያዎች በሰጠችው ቃለ መጠየቅ ላይ ይህንን የመንገድ ፅዳት ሥራዋን ለአንድ ዓመት እንደሠራችው እና እንደሞትወደውም ጭምር ትናግራለች።
ሰው ለእርሷ ባሳየው ፍቅርም መገረሟን ስትናገር “እንዲህ ዓይነት ሁኔታንም እንዳልጠበቀች ተናግራለች።

ታድያ የዚህ ቪዲዮ መነጋገሪያ መሆን እና ብዙ ሰዎች ጋር መድረሱ እንስቷን ታይላንድ ውስጥ ‘ኖንግ’ በመባል በሚታወቅ ትልቅ የሜካፕ አርቲስት በሚያዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ተጋብዛለች።

ዕድለኛዋ እንስት ለ‘ኖንግ’ የኮስሞቲክስ ብራንድ ሞዴል ሆና መሥራት የጀመረች ሲሆን ከሌሎች ትላልቅ ብራንዶችም ጋር በጋራ ለመሥራት ጥያቄዎች እየቀረቡላት ነው።
እርሷም እንደተናገረችው ከሆነ እስካሁን ትሠራ የነበረውን የመንገድ ላይ ፅዳት አቁማ ሙሉ ጊዜዋን እና አትኩሮቷን አዲሱ ሥራዋ ላይ እንዳደረገች ተናግራለች።

credit : etvet


AD



የደራው ላይ ያስተዋውቁ ገበያዎን ያድሩ!

ያግኙን : 0919474444


AD

በአንድ ብር መልዕክት ለልጆች ተስፋን እንለግስ

9923 OK ብለው ይላኩ



ሙዳይ የበጎ አድራጎት ማህበር
MUDAY CHARITY ASSOCIATION

ተስፋን እንለግስ



ወደብ ማግኘት

ሠሞኑን የሚናፈሠው ይሄ ወሬ ብቻ ነው እንግዲህ ትንቅንቁ ሁሉ ወደብ ወይም ሞት ሆኗል።ኢትዮጵያ እራሷ የሞታስተዳድረው ወደብ ስለሌላት ብቻ በአመት የሞታወጣው ወጪ ቀላል እንዳይመሥላችሁ ወጪውን ተዉት የወደብ ነፃነት ስለሌላት ብቻ የወጪ ገቢ እቃዎችን በባዕድ አገራት እንዲታይ ሆኗል።ወደብ የሌላቸው ሀገራት ወደብ ካላቸው ሀገራት ኢኮኖሚያቸው በ25% ይመታል።ይህም የሚሆንበት ምክንያት የወደብ ተጠቃሚ ሀገራት እንደሚያደርጉት ወጪ ገቢ ቁሣቁሶችን በተገቢው ፍጥነት ስለማያንቀሳቅሱ ነው።የዋጋ ንረትን በመከላከልም ረገድ ወደብ ያላቸው ሀገራት የሸቀጥ ታሪፋቸው ውስጥ ወደብ ላይ ያለውን ውጣ ውረድ ስለሚቀንስላቸው ነው።ታድያ ሁሉ ጥቅማ ጥቅም በአንድ ታሪክ አጋጣሚ ያጣችው ኢትዮጵያ እንዴት ባለ ወደብ ሆና ኢኮኖሚዋን ታስተካክላለች ለሚሉአካላት በመጀመሪያ አለምቀፍ ህጉ ምን ይላል የሚለውን ማየት ተገቢ ነው።በጥቅሉ ህጉ የሚለው”ወደብ ካላቸው ሀገራት አጠገብ ያለ ማንኛውም ሀገር በሰጥቶ መቀበል መርህ ባለ ወደብ ሀገር የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ድርድር በማድረግ እና ለባለ ወደብ የተለያዩ ጥቅም የሚያገኝበትን አማራጭ በመስጠቅ በሞላሹ ደግሞ ወደብ የሚያገኘው ሀገር በወደቡ በነፃነት እንዲጠቀም ያደርጋል”ነው የሚለው።

ከዚህ ውጪ በሀይል የተደረገ ወደብ የማግኘት ጉዳይ እምብዛም በአለም ላይ የተለመዱ አይደሉም በታሪክ ወደኃላ መለስ ብለን የምናያቸው እንዲህ አይነት ኩነቶችም ቢሆኑ የረጅም አመት ተጎታች ጦስን ይዘው እንጂ ያን ያህል አልጋ በአልጋ ሆኖላቸው እያሥተዳደሩ አይደለም።

ወዲህ ወደ እኛ ሀገር ስንመጣ ዙሪያችን ማለት ይቻላል ወደብ ባላቸው ሀገራት ነው ተከበን ያለነው እነዚህ ሀገራት ለእኛ ወደብ ሠጥተው ሀገራቸውም ተጠቃሚ ሆና እንድትቀጥል የማይሹት ከምቀኝነት እና በሌሎች ኢትዮጵያ እንድታድግ በማይፈልጉ ሀገራት ጫና ላይ ስለሚወድቁ ነው እምቢተኝነታቸው። በተለይ የምቀኝነቱ ጉዳይ ያፈጠጠ እና ያገጠጠ ነው ለብረን እንደግ ሲባል እንዴት ለንተም እኔም ለናድጋትም ተያይዘን እንጠፋታለን እንጂ ይባላል በዚህ ዘመን እኮ በርካታ አብሮ ለማደግ ሌት ተቀን የሚሰሩት ሀገሮች በርክተዋል እንጂ ለንተም በርህን ዝጋ እኔም ከርችሜ ህዘባችንን እናሠቃይ የሚል ሀገር የለም የእኛ ለካባቢ ሀገራት ግን ግን ኢትዮጵያ ወደብ ሣይኖራት ከችግር ለመውጣት ይህን ያህል ከተንደረደረች ቢኖራትማ ለታኖረንም የሚል ምቀኝነት ውስጥ ነው ያሉት።
አሁን ደግሞ ወደ ሦስተኛ ሀገራት ጫና ልውሰዳችሁ ግብፅ በዚህ ቀጠና ምን ያላደረገችው ነገር አለ?የያዘ ይዟት እንጂ ነፃ ብትሆን ይሄኔ ተጨማሪ ስንት ነገር አድርገው ነበር ግን ምን ዋጋ አለው ፈጣሪ ሰላምሽ ይታወክ ሲላት ከጎኗ ባለችው እስራኤል ሠጊሚን ለጥታለች።እንደዛ ባይሆን በለንድ አመት ውስጥ ኢትዮጵያ የሚያዋስኑ ሀገራትን ለስሬ እየጎበኘች እቺን ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር በእናንተ አማካኝነት ወጥሬ ልያዛት እያለች ተውተርትራለች።



ሀገራችን እንዳለመታደል ሆኖ በጎ የሚባል ጎረቤት የላትም።ቢኖር እንኳን በጥቅማጥቅም እየተደለሉ ከጉርብትናው ይልቅ ፍራፋሬው አመዝኖባቸው ሰንቴ ከድተውናል።በአለም ላይ ከግጭት አትውጪ ተብላ የተረገመች ይመስል በውስጥም ልጆቿ በግጭት ውስጥ መሆናቸው ለውጪ ጣልቃ ገብነት ትልቅ አስተዋፅዎ አድርገዋል።አንዳንድ ኢትዮጵያን የሚጎበኙ ሀገራት የመጀመሪያ ጥያቄያቸው ለምን የውስጣችሁን ሰላም አስተካክላችሁ ከውጪ የሚመጣውን ውርጂብኝ በጋራ የማትመክቱት ይላሉ ብዙ ጊዜ ያላስተዋሉት በባንዳነት የሚንቀሳቀስ ሀይል እያለ በሰላም ለመኖር መቸገር እንዳለ አለማወቃቸው ነው።ይሄማ ባይሆን ይሄኔ የትና የት ደርሰን ነበር ታሪካዊ ጠላቶቻችንም እነርሡ ባይተማመኑ ፈፅሞ አይደፍሩንም “በጥባጭ ካለ ማን ጥሩ ይጠጣል” እንደሚባለው በቃ የእኛ የወደብ ማግኘት ሠላማዊ እንቅስቃሴ ቤታችን ውስጥ ባሉ ልጆች ሂደቱ እንዳይፋጠን ሆኗል ለማለት ነው።አንዳንድ ጊዜ ለሀገር ጥቅም ነው የምንታገለው የሚሉ አካላት ዞር ብለው ቢያዩ ብለን የምናስበው የሀገር ብሔራዊ ጥቅም አጣብቂኝ ውስጥ እየገባ እነርሱ በቻሉት መጠን ትግላቸው ውጤት አምጥቶ የሆነ የሚፈልጉት ቦታ ቢደርሱ የተበላሸውን ነገር እንዴት አድርገው ነው ማቅናት የሚችሉት?በኢትዮጵያ ውስጥ አልተበደልኩም የሚል ብሔር እና ክልል የለም አንዳንዴማን ተበዳይ ሆኖ ማን በዳይ እንደሆነ ግራ ይገባል ።ይህንን ቀውስ እንኩዋን ለማስተካከል ይጥራሉ የተባሉት ምሁራን እና ፖለቲከኞችም እነርሡ ራሣቸው በየጎሬያቸው ገብተው ለአካባቢያቸው እንጂ ለሌላው ግድ እንደሌላቸው ነው የሚታዩት እስኪ ለሀገሬ ግድ ይለኛል የሚለውን አክቲቪስት አልያም ፖለቲከኛ ጋዜጠኛም ሊሆን ይችላል ተመልከቱት የሚያወራው ሀገር ወዳድ መሆኑን ነው ግን ከሌሎች ኢትዮጵያን ከሚጎዱ ሀያላት ጋር ግን ሲወግን ይታያል።

#Atrf Newspaper,Washington Dc


Ethiopia
LAND OF ORIGINS
ETHIOPIA
LAND OF ORIGINS
VISIT ADDIS, AFRICA'S DIPLOMATIC CAPITAL





አብረን ስንሆን ያምርብናል!

ከሳምንት የቀጠለ

ሓጂ ቱሬ የመርካቶ አምባ

“ትምህርት ለሁሉም ነገር መፍትሄ ነው”

ሓጂ ክፈር ቀዳጅነታቸው ጋር በትምህርት ጠቃሚነት በእጅጉ ያምናሉ፡ ፡ ወሂብ ሲናገር “አባቴ መስገድ እና ትምህርት ቤት ያልሰራበት ቦታ የለም! ትምህርት በጣም ነበር የሚወደው። ትምህርት ለሁሉም ነገር መፍትሄ ነው ብሎ ያምን ነበር። የሚገርማችሁ ከ20 እስከ 30 ለሚሆኑ ትምህርት ቤቶች በተለያየ አካባቢ ደሞዝ ይከፍል ነበር። ያገኘውን ሁሉ “ትምህርት ቤት ክፈቱ እረዳችኋላሁ ይል ነበር።” ታዲያ ራሳቸውን እንዲችሉም የተለያዩ ገቢ ማስገኛ ንግዶችን ይፈጥሩላቸው ነበር።



አንዷ ሃምሳ ያህል የብሎኬት መሥሪያ ማሽን ከቆጵሮስ አስመጥቶ ለተለያዩ ት/ቤቶች አከፋፍሏል። ከዚህ በተጨማሪ አባቴ ዝም ብሎ ደሞዝ የሚቆርጥላቸው ብዙ ሰዎች አሉ፤ አሁን እሱ ከሞተ በኋላ እንኳን ብዙ ሰዎች በተለያየ ጊዜ እየመጡ “አባታችሁ ደሞዝ ይቆርጥልን ነበር” ይሉናል” እኛም አባታችን የጀመረውን ደሞዝ ማቋረጥ ስለማንፈልግ እንከፍላቸዋለን።”

በርካቶች ስለ ሓጂ የሚያውቁት ሌላ ልዩ ታሪክ አላቸው። ሃጂ ለበርካታ ዓመታት በረመዳን ፃም ወር ብዙዎችን ችግረኞች ሰብስበው ጾሙን አብረው እየጾሙና እየመገቡ የረመዳንን ወር በጋራ ያሳልፉ ነበር; : በረመዳን ወር በሓጂ ግቢ ውስጥ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ወረን ሲያሳልፉበአንድመንደርውስጥሊከሰቱየሚችሉነገሮችሁሉይከሰታሉ፡ : ሕጻናት የሚወለዱበት፤ አንዳንዴም ሰዎች የሚታመሙበትና፤ በደክተሮች ታክመው የሚድኑበት እና አልፎ አልፎም የሚሞቱበት ብዙ ነበር። ወሂብ ስለ ሁኔታው ያስታወሳል::

“ከ5 ሺህ ያላነሰ ሰው በረመዳን ወር እዛው እቤታችን እያደረ እየዋለ ያሳልፍ ነበር። እኔ ስለ አጀማመሩ አላውቅም በወቅቱ አሜሪካ ነበርኩ፤ ግን ነገሩ በትንሽ ሰው እንደተጀመረ አውቃለሁ። ሆኖም በሂደት ግን አምስት መቶ፣ አንደ ሺ፣ ሁለት ሺህ እያለ ቁጥሩ ጨመረ፡ : በአንደኛው ዓመት የመጣ ሰው በሚቀጥለው ብዙ ሰው ሰብስቦ ይመጣ ነበር። ከሁሉም አካባቢ ነበር ሰው የሚመጣው እንደውም እኛ መጨረሻ ላይ ከአዋሽ ወዲያ እንዳይመጡ እናሳስብ ነበር። ነገር ግን ሰው እስከቆመበት ጊዜ ድረስ ከሁሉም አቅጣጫ ይመጣ ነበር፡ :”

የሓጂ መልካም ተግባር ብዙዎችን ከጎናቸው እንዲቆሙ የሚያነሳሳም ነበር። “ነገሩ ባባቴ ይጀመር እንጂ ብዙ ጥሩ ሰዎችም በገንዘብም በጉልበትም በመርዳት ይሳተፋ ነበር። ሰው በጣም እየበዛ ሲሄድ እዛው የሚወልዱ፣ የሚሞቱ እና የሚታመሙ ሰዎች ይኖሩ ጀመር ከዛም አባቴ ለምን ዶክተር አንቀጥርም ብሎ ፈልገን አንድ ዶክተር አገኘን፤ እሱም በጣም ጥሩ ክርስቲያን ሰው ነበር።

አባቴን “ይህ ሁሉ ደሃ እርስዎ ሰብስበው እያበሉ እያየሁ እኔ በገንዘብ አልሰራም!” ብሎ ብዙ ዓመታት ከኛ ጋር በነፃ ያገለግል ነበር። በጣም ጥሩ ሰው ነበር። በጣም ብሶባቸው ያገኛቸውን ታማሚዎች በእርሱ አማካኝነት እስከ ጀርመን አርድረስ ሄደው እንዲታከሙ ተደርጎ ነበር። :”

ሓጂ ቱሬ የቻይና ኤምባሲ ሓጂ ለቻይና ለየት ያለ ስሜትና ፍቅር አላቸው፤ ጠንከር ያለም ትስስር አላቸው። ከርሳቸው በፊት የነበሩ አውሮፓውያን ነጋዴዎች ዕቃዎችን የሚያስመጡት ከአውሮፓ ነበር።

ሓጂ የቻይናን የገበያ መስመር ከቀደዱት ገዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ነጋዴዎች እና ቻይና የበለጠ እየተቀራረቡ ሄደው ዛሬ አገራችን ከፍተኛውን እና ከአምስት ቢሊየን ብር በላይ የንግድ ልውውጥ የምታደርግበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።





በአንድ ወቅት የሐጂ ቤት የቻይና ኤምባሲ የሚል ቅጽል ስም ሁላ ተሰጥቶት ነበር። ያለ ምክንያት አልነበረም፤ በወቅቱ ተጠቃሚዎች ለቻይና እቃዎች ብዙም ፍላጎቱ አልነበራቸውም፤

ሓጂ እንዴት የቻይናን ዕቃዎች በሀገር ውስጥ ተጠቃሚ አሰለመዱ?

“አባቴ የቻይና ዕቃዎችን ሲያስመጣ ቀጥታ ፈላጊዎቹ የሚገኙበት ቦታ እየሄደ ሞክሩት ይላቸዋል። ለምሳሌ የቻይና _ ኤሌክትሮድ _ ሀገር _ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስገባው አባቴ ነበር። ከዛም በየጋራዡ እና ብረታ ብረት ድርጅቶች በመሄድ _ ኤሌክትሮዶቹን እንዲሞክሩት ይሰጣቸው ጀመር፤ _ በመጨረሻ ተጠቃሚዎች በዋጋ የቀነሰ አገልግሎቱም ጥሩ የሆነ ምርት ሲያገኝ አባታችን ወደሚያስመጣቸው ምርቶች መዞር ጀመሩ።

“አባቴ _ ከምስራቅ _ አውሮፓ _ ከሚያስመጧቸው ዕቃዎች በተጨማሪ ከቻይና ዕቃዎችን ማስመጣት የጀመሩት እሳቸው ናቸው። የቻይና ኤምባሲም ታላቅ ወዳጃቸው በመሆን ያባቴን እግር ተከትለው ቻይና ለመነገድ ለሚፈልጉ ሰዎች የቻይና ኤምባሲ ቪዛ ለመስጠት መረጃ የሚወሰደው ከአባታችን ነበር፡ ፡ በዚህ ምክንያት እቤታችን የቻይና ኤምባሲ የሚል ቅጽል ስም ሁሉ ወጥቶለት ነበር።” (ሳቅ)

ቱሬ ኩባንያ ከሓጂ በኋላ
******

“አባታችን እና ድርጅቶቻችን የሚታወቁት በብዛት በአስመጪነት ንግድ በመሰማራታቸው ነው። አሁን ግን ከዚህ በተለየ መልኩ ወደ ኤክስፖርት እና ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ፊታችንን አዙረናል፡ ፡ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ በቱሬ ስም፤ በግላችንም እንዲሁም ከቻይና ኩባንያዎች ጋር በጥምረት እየሠራን ነው ያለው፡ ፡ በተለይ በቢንቢ ምርት ላይበስፋት እየሠራን ነው። የአባቴ ህልም ፋብሪካ መገንባት ነበር እሱን ለማሳካት እየሮጥን ነው። አባታችን “ሲሚንቶ ፋብሪካ ክፈቱ ክፈቱ እንዳለ ሳያይ ነው የሞተው አሁን ግን የሲሚንቶ ፋብሪካ ከፍተናል።”“

“አሁን የአባታችን ይሰሯቸው የነበሩትን ሥራዎች በአመዛኙ እየተነውናቸው ነው ማለት ይቻላል፡ ፡ ባሁኑ ጊዜ የምንሠራው ፋብሪካ ማስመጣት እና ማማከር ነው። ብዙ ባለሀብቶች ገንዘብ ኖሯቸው ምን እንደሚሰሩ ማወቅ ግር ይላቸዋል፤ እኛ ጋር ሲመጡ ምን መሥራት እንዳለባቸው ሃሳብ እንሰጣቸው እና ወደ ሥራ እናስገባቸዋለን።

“በአሁኑ ወቅት ሦስት የሲሚንቶ ፋብሪካ አለን። ሁለቱ ካፒታል እና ፓዩኒር የሚባሉት ከቻይናዎች ጋርበጥምረት የከፈትናቸው ናቸው። አንድ በቱሬ ስም ቤተሰብ ብቻ ያለበት ያባታችን ወንድሞችም ጭምርያሉበት ፍብሪካ ነው። ሌላ ደግሞ ወደ ፓኬጂንግም ገብተናል።”

ሓጂ በቤተሰብ ውስጥ
******

“አባታችን ሰውን በፍቅር መያዝ ነው የሚወዱት፤ በፍቅር እንድትሠራ ነው የሚፈልጉት፤ ሥራ ካልሠራህ ብለው ሰው ማስጨነቅ አይወዱም፤ የሚያስጨንቅም ሲገጥማቸው ደስ አይላቸውም፡ : “ተው አታስጨንቀው ሰው እንደጠባየ እና እንደፍላጎቱ ነው መኖር የሚገባው ደሞ እኛ እየሠራን አይደለም እንዴ?! ሁሉም ሰው የግድ መሥራት የለበትም!” ይላሉ።

አባታችን ዕረፍት የለውም ሥራ በጣም ነው የሚወደው። የሚገርህ ሁሉም ቤተሰብ እንቅልፍ ብዙ አይተኛም እኔም አሁን እራሴን ሳውቅ በቀን ውስጥ በጣም ትንሽ ነው የምተኛው። የቀን እንቅልፍማ አይታሰብም።

ሃጂ ዘጠኝ ልጆችን ወልደዋል። ወሂብ የሦስት ልጅ አባት ነው። ሁለት ወንድ ልጅ እና አንዲት ሴት ልጅ አሉት። ልጆቹም የእሱን እግር ተከትለው በቤተሰቡ ቢዝነስ ውስጥ አሻራቸውን እያስቀመጡ ነው። አባቱ እንዴት እንዳሳደጉት ወደ ኋላ ተመልሶ እንዲህ ያስታወሳል።

“አባቴ ፍፁም ክፋት የማያስብ፤ የሠራ ሰው እና ሀገር ወዳድ ነው። እኛ ገና ልጆች እያለን ሱቅ ነበረው፤ እሱም ጎረምሳ ነበር። የሚገርምህ በቂ ገንዘብ ኖሮት እንኳን ከሰፈሩ ህፃናት እንዳይለየን ብሎ የተለየ ነገር ገዝቶልን አያውቅም። የተለየ ነገርአልገዛም ጓደኞቻችሁን ምሰሉ ይለን ነበር። በቃ እንደማንኛውም ሰው እኩል ሆነን እንድናድግ ነበር ፍላጎቱ።

ሓጂና ይቅርታ
******
ሓጂ የይቅርታ ሰው ናቸው። በይቅርታቸው የልጃቸውን ሕይወት የመለሱበት ሁኔታ ለቤተሰባቸው መሰረታዊ ፍልስፍና ትኖ ያለፈ አጋጣሚ አለ። ከልጆቻቸው አንዱን ወደ አሜሪካ ልከው እጅግ በርካታ የሚባል ባለ ሰባት አሃዝ ዶላር ባንክ ውስጥ አስቀምጠውለት ትምህርትህን ቀጥል ብለው አያያዙት። ጎረምሳው

ግን አሜሪካንና ዶላርን ይዞ ወደ ትምህርቱ መግፋት አልቻለም። ለትምህርት የተቀመጠው ገንዘብም እንደጨው ሚሟና አጅሬው ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ። ሓጂ ልጃቸው ለእረፍት እንደመጣ አስበው የተለመደውን ፍቅራቸውን እና እንክብካቤያቸውን ሲመግቡት ቆዩ፤ ጎረምሳው ግን ተመልሶ የሚሄድ አልሆነም፤ አንድ ቀን ሲብስባቸው “አንተ አትሄድም እንዴ ወደ ትምህርትህ?“ ሲሉ ይጠይቁታል፡ : ምላሹ ግን አናት ማከክ ሆነ፤ ሓጂም ነገሩ ገባቸው፤ “ገንዘቡንስ አጠፋ ው?” አሉ። በድንጋጤ የተዋጠው ጎረምሳ ልጃቸው አዎ ለማለት ድፍረት ባይኖረውም _ አላጠፋሁትም የማለት አቅም ግን አልነበረውም። “ይሁን እንግዲህ አሉ ሓጂ እንኳን አንተ አልጠፋህ ነገ ስርተህ ታመጣዋለህ አንተ ብትጠፋ ግን ማን ፈልጎ ያመጣሃል?” አሉት፤ ያ ጎረምሳ ዛሬ እሳቸውን ተክቶ ድርጅታቸውን ይመራል።

የሐጂ ስንብት
*****
“አባታች በ86 ዓመቱ ነው የሞተው፤ እኔ የሚገርመህ በዕጣ ፈንታ አምናለሁ። አባታችን ቻይናን በጣም ነው የሚወዳት፤ የህይወቱም አንድ አካል ሆና ነው የኖረችው። በሕይወቱ የመጨረሻ ወራት እስኪ ቻይና ወስጄ ላዝናናው ብዬ አሰብኩና ተያይዘን ሔድን፡ :

ከቤይጂንግ የአራት ቀን መንገድ የሚጠይቅ ቦታ ተጉዘን ስንንቀሳቀስ በድንገት ታመመብኝ። በጣም ደነገጥኩኝ። ወደተገኘው ሆስፒታል ወሰድኩት፡ ። ሕክምናው ግን ጥሩ አልተከናወነም እና አባቴ በሰው አገር አረፈ። በጣም ደነገጥኩኝ። በወቅቱ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በየቀኑ በረራ አያደርግም፤ ከዛች የክፍለሃገር ግዛት ከመጣሁ በኋላ እንደገና ቤየጂንግ ብዙ መቆየት ነበረብኝ፤ የአባትህን አስከሬን ይዘህ ብቻህን በሰው አገር መሰንበት ቀላል አደለም፡ ። በአስራአንደኛው ቀን አስከሬኑን ይዤ ስነሳ እቤት አጎቴ ጋር ደውዬ “ኤርፖርት ጠብቁኝ፣ ሬሳ ይዤ ነው የምመጣው፣ አባታችን አርፏል፤” አልኳቸው፤ ምን ያህል መደናገጥ ሊሆን እንደሚችል አስበው።”

አሁን መርካቶ ይበልጥ መንቃት ጀምራለች እኛ እና ውሂብ ከተሰበሰብንበት ጠረጴዛ ዙሪያ በርካቶች ወሂብን ፈልገው የሚመጡ ባለጉዳዮች ወጣ ገባ ማት ጀምረዋል። በጸሃፌና በተራ ባለጉዳዮች የማይሰተናገዱባት የትላትናዋ የሓጂ ቢሮ የዛሬዋ የወሂብ መቀመጫ መጨናነቅ አበዛች። ከወሂብ ጋርየነበረንን አስደሳች ቆይታ ቋጨን።

የሓጂ መልካም ስብዕና በሁሉም የቤተሰብ አባል ላይእንዳረፈ ብዙ ሁኔታዎች በግልጽ ይናገራሉ። ወሂብ እና ወንድሞቹ የሓጂን የፋብሪካ ህልም እውን ለማድረግ በድሬዳዋ አካባቢ በዓይነቱ እጅግ ግዙፍ የሆነ የኢንዱስትሪ መንደር ለመገንባት ወደ እንቅስቃሴ ገብተዋል።

ከመቶ በላይ የቻይና ባለሃብቶች በዚህ የኢንዱስትሪ መንደር ግዙፍ ፋብሪካዎችን ከሌሎች የሀገር ውስጥ ባለፋብሪካዎች ጋር በጥምረት ይገነባሉ። እኚህ ፋብሪካዎች የኢንዱስትሪ መንደሩን ከማሞቅ በዘለለ የሀገሪቷን ኢኮኖሚም የማሞቅ ሥራ ይጠበቅባቸዋል።

በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች የሥራ ዕድል በሚያገኙበት በዚህ የኢንዱስትሪ መንደርየሓጂ ሕዝባዊነት በሁሉም ጎኑ ፍሬ ማፍራቱ ሲታይ እነወሂብም የአባታቸውን የህልም አደራ እየተወጡት እና ቱሬ ኃ. የተ. የግ. ኩ. እያሰፋትና እያደራጁት ይገኛሉ።

ሓጂ ቱሬ ዛሬ በሕይወት የሉም፤ ነገር ግን ልጆቻቸው አባታቸው የተመኙትን ሁሉ እየሆኑላቸው በአገራችን በተምሳሌነቱ በግንባር ቀደም ደረጃ ተጠቃሽ ከሆኑት የቤተሰብ ቢዝነስ ውስጥ አንዱ የሆነው ቱሬ እና እየገሰገሰ ይገኛል።

የሓጂን ነገር እዚህ ጋር ደመደምን!!


credit : ohad benami



በላዲ መኪሲኮ

ZAMRAN STUDIOS

100 ብር ብቻ



1 ሰው በላዲ

ሜክሲኮ በላዲ

ሰሰ 25111

SE



Big Habesha

የሙዚቃ ኢንዱስትሪው የንግድ ጦርነት (Apple music VS Spotify)

Part 1

ማርቲን ሎሬንዘንና ዳንኤል ኢኬ የተባሉ ሁለት ስዊድናውያን የቴክኖሎጂ ስራ ፈጣሪዎች በ2008 ዓ.ም Spotify የተባለ የሙዚቃ streaming service ለአለም አስተዋወቁ።

በጊዜው ስራውን ሲጀምሩ የተጠናበትና ብዙ ተጠቃሚዎችን ሊያስገኝላቸው የሚችል የmarketing strategy ተጠቀሙ። ይህም ሰርቪሱን በሁለት መንገድ ለተጠቃሚዎች ማድረስ ነበር። የመጀመርያው ዝቅተኛ ገቢ ላለውና መክፈል ለማይችለው የማህበረሰብ ክፍል የተወሰኑ ፊቸሮችን በመቀነስና መሃል ላይ ማስታዎቂያዎችን በማስገባት ሙዚቃውን በነጻ ማቅረብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ መክፈል ለሚችሉት ያለማስታወቂያ በpremium service ሙዚቃውን ያለገደብ ማቅረብ ነበር። ይህ strategy ስለሰራላቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤታማ መሆን ቻሉ።

ይህ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ ከአለማችን ትልቅ የቴክኖሎጂ ድርጅቶች መካከል አንዱ የሆነው Apple ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ iTunes የተባለ የሙዚቃ ማጫወቻና መግዣ software ነበረው።



ይህ ሶፍትዌር ሁለት ክፍተቶች ነበሩበት። የመጀመርያው ሶፍትዌሩ የሚሰራው በአፕል እቃዎች ላይ ብቻ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ሙዚቃ ለማዳመጥ ግዴታ እያንዳንዱን ሙዚቃ መግዛት ብቸኛ አማራጭ ነበር።

Spotify እነዚህን ሁለት ክፍተቶች ተጠቅሞ በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ በ2015 ዓ.ም ከ75 ሚሊዮን በላይ ተጠቃሚዎችን ማግኘት ቻለ።

ይህን እድገት ያስተዋለው Apple በ2015 iTunesን rebrand በማድረግ ወደ Apple music አሳደገው። አፕል የበጀት እጥረት የለበትም፤ ከፍተኛ የሆነ የiPhone ተጠቃሚ community አለው፤ በተጨማሪም አለም ላይ አሉ ከተባሉ ሙዚቀኞች ጋር ስምምነት ላይ ደርሷል። በነዚህ ምክንያቶች የApple አመራሮች Spotifyን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከገበያ እንደሚያስወጡት እርግጠኞች ነበሩ።

Apple በዚህ ብቻ አላበቃም spotifyን በተመለከተ አንድ አደገኛ ውሳኔ ወሰነ።

ክፍል ሁለት ሳምንት ይቀጥላል


Bored
Cellphone
Addis Ababa

ጣዕም ሬድዮ የቴሌግራም ቦት

ጣዕም ሚዲያ የቴሌግራም ቻናል





. ለአጠቃቀም ቀላል እና በአማርኛ ቋንቋ የቀረበ
. 24/7 በጥራት ማድመጥ የሚያስችል

taem ጣዕም @taemmedia

. በድምፅ እና በፅሁፍ አማራጭ የሚቀርብበት
. በማንኛውም ጊዜ ለመስማት Download የሚደረግ




ዕሮይ
ኣትጠልቕዎ
www.yederaw.com